# ደወል ተደውሏል

ከነቅዓ ጥበብ

እኒያ መጣፍ ገላጭ፣ ደብተራ መንበሩ፣
የቤተክህነትን፣ ኮከቡን ሲቆጥሩ፣
ሴት ታሰጋዋለች፣ ብለው ተናገሩ። (ብእሲት ታፈርሆ)

እንደ ዮዲት ጉዲት፣ ሲደፈር ታቦቱ፣
ዘንድሮ እጅጋየሁ፣ በቤተክህነቱ።

መናኙ አባታችን፣ ሰግደው ሲማለሉ፣
በጣም ተፈታታኝ፣ እጅጋየሁ አሉ።

ይቺ ክፉ ጋኔል፣ አሳሳች ፍጥረት፣
ለማንንም አትበጅም፣ እጅግ ክፉ ናት፣
ባል አክብራ አታውቅም፣ ላያሌ ዓመታት።

“ቅዱሱ” አባታችን፣ የኛ ነጭ ለባሹ፣
ምነው አላልቅ አለ፣ ቢዋሹ ቢዋሹ፣
ወደ አስኪማቸው፣ ይሻላል ቢሸሹ። (ቆባቸው)

የድንግሏን መቅደስ፣ ደም እያፈሰሰ፣
ወንበዴው አባት ነው፣ ህጓን የገሰሰ።

አባቶች ስትመክሩ፣ ጅምር ስትወጥኑ፣
ለምትበልጠው ፀጋ፣ ለአስኪማችሁ ቅኑ፣
ጅምሩን ተልዕኮ፣ ስታጠናቅቁ፣
አባቶች አደራ፣ ቅናቱን አጥብቁ። (ቅናተ-ዮሐንስ)

በመነኩሳት ገድል፣ በነገረ-አስኪማ፣
የሞተ ሲፈራ፣ ዘንድሮ ተሰማ።

የቤተክርስቲያንን፣ ታሪክ ለሚረዳ፣
ሰቃይ ለቄርሎስ፣ አይደለም እንግዳ፣
ይብላኝ ለሆዳሙ፣ ዳግማዊ ይሁዳ።

አይዋ ሀብታሙ፣ ቤተክህነታችን፣
በቂሙ ተፈታ፣ በአባቶቻችን።

የሲኖዶሱ ምርት፣ ሲጠበቅ የኖረ፣
አራት ኪሎ ብቻ፣ እንደሆነ ቀረ።

ካህናት፣ ምዕመናን፣ ፀሎት ያለባችሁ፣
ደወል ተደውሏል፣ ንቁ ከእንቅልፋችሁ!